# [illegible]

ቁ.7
23/12/

## ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ዲሞክራሲ ባለፈው ቁጥሩ /6/ አሁን ያለው ሥርዓትና መንግሥት የታላላቅ ባለመሬቶችንና የታላላቅ ከበርቴዎችን ጥቅም ብቻ አስጠብቆ፣ የቀረውን ሠፊውን ሕዝብ፣ሠራተኛውን፣ገበሬውን፣ወታደሩን፣ምሁሩን፣የተጨቆኑት ብሔሮችንና ሃይማኖቶችን፣ሴቶችን፣ በአጠቃላይም የሕዝብ ወገንና ክፍል የሆነውን የሚጨቁን፣ዲሞክራሲያዊ መብቶችን /የመሰብሰብ፣መጻፍ፣የመናገር፣የመደራጀት.../ የሚነፍግና በባላባቶች፣በውጭ አገር ካፒታሊስቶች፣በአገሩ አቀባባዮችና የቢሮ ከበርቴዎች ያለ ቅጥ የሚያስበዘብዝ መሆኑን አመልክተን፣ይህንኑ በማስታከክ ለለውጡ መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን በአጠቃላይ ዘርዝረናል::

በዛሬው እትም በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሰውን የፕሮግራሙን ነጥብ ለማብራራት ይሞክራል:: ባጭሩ፣የተዘረዘረው ፕሮግራም መጀመሪያው ነጥብ 3 መሠረታውያን ሐሳቦችን ያዘለ ነው::

1. ኢትዮጵያን የኢምፔሪያሊስቶች እጅ አዙር ቅኝ ግዛት ያደረገውና የሕዝቡንም መሠረታውያን ዲሞክራሲያውያን መብቶችን በመንፈግና የድህነት ቀንበር በመዝጋት የረሐብና የድንቁርና፣ የበሽታ መደብር ያደረገውን ፈላጭ ቆራጭ ነጋሢ መንግሥት መደምሰስ፣
2. በመሠረቱ ፀረ ዲሞክራሲ የሆነውን፣የሕዝቡን የበላይነት የሚቃወመውን፣የመከፋፈል ምክንያትና ምልክት የሆነውን የዘውድ አገዛዝ ማስወገድ፣
3. መሠረተ ሠፊና ተራማጅ የሆነ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት በመመሥረት፣ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማቋቋም፣ ናቸው::

ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ማለት፣አንድ ሰው ሕዝቡን እንደፈለገው፣እንደፈቀደው የሚገዛበት ሥርዓት ነው::ይህ ዓይነት ሥርዓት በኢትዮጵያ የተጀመረው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በተለይም ከፋሺስት ወረራ በኋላ ነው::ከዚያ በፊት የነበሩት ነገሥታት ለስሙ ሥልጣናቸው ወሰን አልነበረውም ቢባልም፣ይህንን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችላቸው የተጠናከረ መንግሥት ቢሮክራሲም ሆነ ወታደር ስላልነበረ፣ሥራ ላይ አውለውት አያውቁም ነበር::

ታሪክን ስንመለከት የትም አገር ቢሆን ፈላጭ ቆራጭ ነጋሢ አገዛዝ የሚመጣው በመሳፍንት/ባለመሬቶች/ መደብና ይህንን መደብ በሚተካው በከበርቴው መደብ መካከል ያለው የኃይል ሚዛን ተመጣጥኖ በሚመስልበት ጊዜ ነው::ፈላጭ ቆራጭ ነጋሢው ሁለቱን መደቦች እያጋጨና እየሸነገለ በመካከሉ ሚዛን ጠባቂ ባለ ሙሉ ኃይል ሆኖ ይገዛል::

በአገራችን የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ሊጠናከር የቻለው፣በውጭ አገር ከበርቴዎች፣መንግሥታት፣ማለትም፣በኢምፔሪያሊስቶች ድጋፍና እርዳታ ነው::ኢምፔሪያሊስቶች፣ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በፊት ኃይለ ሥላሴ ለየ ለየ መሳፍንትን ለማዳከም የበላይነትን ለማግኘት የሚገለገልበት ገንዘብ፣ጦር መሣሪያና የምክር ድጋፍ ለገሡለት::የፋሺስት ወረራ፣መሳፍንቱን በማዘርጋት፣ቢሮክራሲ በየቦታው በማቋቋም፣ገበሬ መሳፍንትን በመግደልና [illegible] በማጋለጥ ለኃይለ ሥላሴ ፈላጭ ቆራጭነት መንገድ ከፍቶለታል:: ከዚያም በኋላ እንግሊዞችና አሜሪካኖች በተከታታይ ገንዘብ፣ነገሥ [illegible] በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ፈላጭ ቆራጭነቱን ለማጠናከር የሚያስፈልገውን የጦር፣የገንዘብና የፖለቲካ እርዳታ ሰጥተውታል::ኃይለ ሥላሴም በበኩሉ አገራችንን፣በኢኮኖሚ፣በባህልና በፖለቲካ የኢምፔሪያሊስቶች የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት አደረጋት፣በተለይም [illegible] ጦር ሠፈር በአገሩ [illegible] [illegible] [illegible]

[illegible]

አፍሪካ የኤሲያን ሕዝቦች ጥሬ ሀብት ለመበዝበዝ በየቦታው በሚያካሂዷቸው ጦርነቶች ተባባሪ በመሆን ወታደሮቻችን በኮሪያ በአፍሪካ ጎን ተሠልፈው ፣ለነጻነታቸው የሚዋጉትን ሕዝቦች [illegible] [illegible]ቸው እንዲያለቁ አድርጓል::

ሠራተኞቻችን በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደመወዝ በውጭ አገር ባለ ገንዘቦች እንዲበዘበዙ አድርጓል

ነጋዴዎቻችንና ባለ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎቻችን ፣በገንዘብና በዕውቀት ከሚበልጧቸው የውጭ አገር ከበር÷ ~~በአኮሎቶቶ~~ ላይ ያለ ተመሠረተ ውድድር አድርገው ከጊዜ ወደ ጊዜ በማትረፍ ፈንታ እየከሰሩ እንዲሄዱ አድርጓል::

የበሰበሰው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ባህል ፣በፊልም፣በቴሌቪዥን፣በመጽሔትና በሬዲዮ በነጻ ገብቶ መልካም መልካሙን ባህላችንን እየበረዘ እንዲጠፋ ተደርጓል::

ኢምፔሪያሊዝም ጥሬ ሀብታችን ለመዝረፍና ሀገራችን የኢንዱስትሪ ዕቃው መጣያ እንድትሆንለት ቶሎ የሆነ ፣በሕዝቡ ፍላጎት ላይ የተመሠረተና ለሕዝቡ ጥቅም የሚውል ኢኮኖሚ እንዳይገነባ [illegible]ሳለ::ይህንን የተረዱት አገር ወዳዶች ሁኔታውን ለመለወጥ ቢነሡ ፣እነሱን ለማፈን ሲባል የሀገሪቱን የጦር [illegible] ስለ ተቹ ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ፈጽሞ በማይነጻጸር ደረጃ ያስፋፏቸዋል::——ከፈላጭ ቆራጭ ነጋሢ አገዛዝ ጋር ኢምፔሪያሊዝም ወዳጅ አለበት የምንለው ለዚሁ—ነው::

ምናልባት ባሁኑ ጊዜ ሥልጣኑ ከፈላጭ ቆራጭ ነጋሢ እጅ አፈትልኳልና ፣የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ይወድም ማለት አያስፈልገም ይባል ይሆናል፤ ነገር፣

——የፈላጭ ቆራጭ ሕገ መንግሥት አልተነሣም፤

——ፈላጭ ቆራጭ ያወጃቸው ፀረ ዲሞክራሲ የሆኑ

—— [illegible] ሕጎች አሉ፤

/ [illegible] ——ፈላጭ ቆራጭ ይገለገልባቸው የነበረት እንደ [illegible] ፀጥታና እንደ ባንሴር ያሰባሰቡት ፀረ ዲሞ[illegible]ሲና ኢሰብአዊ የሆኑ ድርጅቶች አሁንም ይሠራሉ

ሁለተኛው ነጥብ የዘውዱ አገዛዝ ጉዳይ ነው::

መሠረቱ/ጉዳዩ የመሳፍንት ሁሉ ቁንጮ ነው:: የክብራቸው መለኪያ፣ የኀይላቸው ማረጋገጫም ነው: [illegible] የዘውድ ሥርዓት፣አንድ ሰው በመወለዱ ብቻ ይገዛ የሚባልበት ሥርዓት ይቀጥል ማለት የዚሁ ስንኩል የመሳፍንትን ሥርዓት ከሥር መሠረቱ በመንቀል ፈንታ መሳፍንቱ ከከበርቴው ጋር በመሸን በመሻረክ፣ሕዝቡን ዳግመኛ የሚቸሉበትን ዕድል አንሰጣቸው ማለት ነው::

ለ/ የዘውዱ አገዛዝ በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል በመደብ፣በብሔር፣በሃይማኖት አድልዎ እንዲነገሥ የሚያስችል የመከፋፈል ፖሊሲያትና ፖለቲካ ነው::

[illegible]/ የዘውድ አገዛዝ፣ የሕዝቡን የሥልጣን ሁሉ ምንጭ መሆን፣ የሕዝቡን የበላይነት የሚቃወም [illegible] ስለሆነ፣ ለዚሁ ፀረ ዲሞክራሲ አገዛዝ መናኛ [illegible] ለማቋቋም መቃብር አለዎር ከሚገኙ በ[illegible] ነው::

መ/ ገጉው ነገሥታት [illegible] ከሕዝብ [illegible] መሸከም በኢኮኖ- ሚ ሲታይ [illegible] እጅግ ከባድ ስለሆነ፣ የማያስፈልግ ሸክም ነው::

የዘውድ አገዛዝ ይውደም እያልን የምንለው ለዚሁ ነው::

• የአጼ ዘሮት/ [illegible] 25/55/ በርእሰ አንቀጹ [illegible] በረጅሙ እንደዚያ... ሰጥቶ ... [illegible] [illegible] ነው፤ የኢትዮጵያ ለውጥ እስካሁን [illegible] ለዘ ያደረገውና ለኢትዮጵያ አድናቆትን ያተረፈው..." ይለናል::

ከዚህ በፊት በዚያው ጋዜጣና ጽሑፎች ለኢትዮጵያ ትልቅ አድናቆት አትርፏል ተብሎ ሲነገረን በደንብ [illegible] ሥላሴ "[illegible] ... "[illegible] የአፈር ቃ አባትነት" ይናገሩለት ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ ነጻነት ያደረጉት 'ተጋድሎ" ...ወዘተ.ወዘተ. ነበረ::ለመሆኑ አሁንም ያደነቀን እነዚያው ሰዎች ይሆኑን፤ [illegible]

የፈላጭ ቆራጭን አገዛዝ ሳንገድል የሕዝብ አገዛዝ ለመመሥረት አንችልም፤ የዘውድ አገዛዝን ሳንገድል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መገንባት አንችልም:: የነዚያ ሰዎች አድናቆት ይቀርብን እንጂ፣ባቦያ በነ.

ዲሞክራሲያ ቁ.7

ወደ እናንቀሳቅስ ፍሮ:: [illegible] የሆነ ዲሞክራሲያዊ የሲቪል ሥርዓት

ሥነ ሥርዓት መሠረቱ ሰፊ የመሠረተ ሠፊ [illegible] የሆነ [illegible] ነው::
መሠረተ ሠፊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት [illegible] ማለት ነው::

እስካሁን የነበረውን አሁንም ያለው መንግሥት የጥቂቶች መንግሥት ነው::

——ለነዚህ ጥቂት ሰዎች ዓለት፣ መሳፍንት ፣ የአገባብ ከበርቴና የባር ከበርቴ ወዘተ. አባሎች ለሆኑት ሰዎች ፣ በኢኮኖሚ በኩል ሕዝቡን እየዘረፈ ፣ ሀብት የሚያከማቹበት መንገድ ይከፍትላቸዋል:: ተቃዋሚያቸውን ያጠቃላቸዋል፣ ከበርቀታቸውን በሕግ ያጸድቅላቸዋል ይጠብቅላቸዋል:: አሁን በቅርቡ በደርጉ የተገለጸው የአንበሳ አውቶቡስና [illegible] ሀብት ሰጣት ድርጅት እየተባለ ይጠራ የነበረው ድርጅት አሠራር ለዚሁ ጥሩ ማስረጃ ሊሆን ይችላል:: በነ ራስ መስፍንና በቀረቱ መሳፍንት እጅ የተያዘው ፍርድ ቤት [illegible] ለሳ ጥሩ ምስክር ነው::

——መንግሥቱ የጦር ኃይሉንና የከበር በታችን ያከፋፍላቸዋል፤ ከማገናኘውም ዓይነት ሥራ ነጻ ያደርጋቸዋል::

——የነሱን ባህል የሀገሪቱ ባህል ነው በማለት በሕዝቡ ላይ ይጭነዋል:: ጌቶች የሚያደርጉት መጥፎ ነገር ሁሉ ጌቶች ስላደረጉት ብቻ ጥሩ ይሆናል:: ጌቶች ሲያስገድዱ ያላገቡ ቆንጆዎች ሰው ይገድላሉ፣——ጀግንነት ነው:: ጌቶች የእጅ ሥራ አይሠሩም፣——ጨዋነት ነው::...ወዘተ.ይባላል:: የገባር አሽከር አንገቡ [illegible] ጌታውን ለማምለክ ይባላል::

——ሃይማኖቱን መሣሪያ ያደርጉታል፤ በግድ ፀሎት ይደረግላቸዋል፤ አገርር ፀር ታማኝ [illegible] /ወላጆችን ከአገሩ በታች አስገዛለት /እየተባለ:: ሥርዓቱ እግዚአብሔር በለሆኑ ለንጉሥ ነገሥቱና ለሌሎች ደግሞ እርሳቸው ስለሾሟቸው አንድነትን አቀርቅር በትሕትና [illegible] እየተባለ ለሕዝቡ ቀስም የሚሰበክ ትምህርት ይሰጣል::

መሠረተ ሠፊ የሆነ መንግሥት ሲባል እንግዲህ የጥቂቶችን መንግሥት አፍርሶ የሕዝብ ወገን ሆኖ የሚቆምበት፣ በሕዝብ ፍላጎት ሥር የሆነ፣ ለሕዝብ ጥቅም የሚሠራ መንግሥት ማለት ነው:: የዚሁ መንግሥት ተቀዳሚ ሥራ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ማስጠበቅ መሆን አለበት:: ማለትም

ጠባብን የመናገር፣ የጽሑፍ፣ የእምነት፣ የመሰብሰብ፣ የሙያ ማኅበርና ሌላም ማኅበር የማቋቋም መብቶችን ገለጽ በሆነና በማያወላውል ሕግ ማጽደቅ ነው::

አንዳንድ ሰዎች የነዚህንና የእነዚህ ነጻነትን እንደ ቅንጦት ይቆጥሯታል:: ጥቂቶች ምሁራን የሚያስተምሩት፣ ሠራተኛ [illegible] ሕዝብን ግን ፈጽሞ የማይነካ አስመስለው ለማቅረብ ይሞክራሉ:: የዕድገቱ ከግምት ከመፍረሱ በፊት ፣ በዚያን ጊዜ የመከላከያ ሚኒስቴር ለነበሩት ለጄነራል ዓቢይ [illegible] ከጻፈው ደብዳቤ ፣

> ለጥቂቶች አፍርካቸውና ዐረ መንግሥት ገለ ሰጦች [illegible]
> ነጻነት ሲባል የሀገሪቱ ዕድገት እንዲሰናከል የሚገፋፋበት ቆንጆ
> የለም::ይላል::

የመናገር ነጻነት ቢኖር በ[illegible] የሚኖር ሕዝብ፣በደሉን፣በተገፈፈበት፣በበሽታ [illegible]...ወዘተ. በረሃብ እንደዚያ [illegible] ሞቶ ባልቀረ ነበር:

የጽሑፍ ነጻነት ቢኖር [illegible] ሕዝብ እንደ ቅጠል ከረገፈ በኋላ ትልቅ [illegible] የመንግሥት ባለ ሥልጣን በ[illegible] ዘገባ [illegible] በድፍረት [illegible] ከ[illegible] ለማስተካከል ከቀከረ በኋላ ምንም [illegible] ይቆጠር ነበር!

የመሰብሰብ ነጻነት ቢኖር ባለ ሥልጣናት ሕዝቡን [illegible] ሲያሠሩት [illegible] ዝም ይባል ነበር:

የአሠራር ፣ የመሰብሰብ ነጻነት በኛ ባለሥልጣኖች ገበሬውን ፣ ተማሪውን፣ሠራተኛውን በየጊዜው በጎዳት እየደበደቡ በበትር እንደሚመሩ ሥልጣን ላይ ለመቆየት ይችሉ ነበርን!

——ታዲያ ይህ ሁሉን ሕዝብ አይመለከተውም!
——የኢኮኖሚ እድገትን አይመለከተውም!
——የፖለቲካ ነጻነትና የኢኮኖሚ እድገት ፍጹም የተቆራኙ፣[illegible] የማይለያዩ አይደሉምን!

ያለ ቀንበር፣ የሐሳብ፣ የጽሑፍ ፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት ነጻነት፣

ሀ/ሕዝቡ በአገሪቷ የእድገት ሥራዎች ለመካፈል የሚኖረውን ፍላጎት ከፍ ያደርጋል፣
ለ/የሕዝቡንና የግል ሰቦችን አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠር ችሎታ ያጎለምሳል፣
ሐ/በሕዝብ መካከል የሚነሡት ልዩ ልዩ ቅራኔዎች በጊዜው መፍትሔ እንዲያገኙ ይረዳል::

አንዳንድ ሰዎች ሐሳብ የመግለጽ ነጻነትን ቀን የጣለውን ከመንቀፍ ጋር ያምታታሉ:: ቀን የጣለው ወይንም ዐቅም ያነሠው በሬሳ ቍራ ጊዜስ ቢሆን እስከሚታክት ድረስ ይፈነጭበት ይችል አልነበረም!

ሰዎች ደሀ ስለሆኑ ብቻ ይህ እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው ለምን ይታሠራሉ በለው ተማሪዎች ሲሠለፉ " የድንፍርና ሠልፍ " ተባለ:: የታነሣሡ አለ ዕቅድ የደረበው ተማሪዎች በከፈቱት ጥቃት ምክንያት ነው ተባለ::እነ ደጃዝማች ታከለ እንኳ ከሀዲዎች ተባሉ::——ሐሳብ የመግለጽ ነጻነት ይህ አይደለም::ሐሳብ የመግለጽ ነጻነት ማለት ሥልጣን ላይ ያለውንም ጭምር ሲያጠፋ መውቀስ ማገለጽ መቻል ማለት ነው::

ደርጋችንም ቢሆን ነጻነትን የሰጠነው፣ የደርግ ባለ ሥልጣኖችን ለመውቀስ ለመክሰስ ለመተቸት ነጻነት አላችሁ በማለት ይመስላል::ካልሆነማ ባንሩሩ ለምን አይነሣም ! የሚደበቅ ከሌለማ ይህን ያህል የወረ ፍርሐት ከየት መጣ! ስንኳንስ ፣በተራማጅ ግለ ሰቦችና ቡድኖች የሚሰነዘሩ ወረቀቶች እንዲታተሉ፣ትላንት ተማሪን ሲገድሉ ፣ሲያፍኑ፣ንብረቱን ሲገርፉ የኖሩትን የፀጥታ ባልደረቦችንስ ማዘዝ እንዴት ነው፣

ሌላው ዓብይ የፖለቲካ መብት የፖለቲካ ፓርቲዎችን የማቋቋም መብት ነው:: የፖለቲካ ፓርቲ የማቋቋም መብት መሠረታዊ ዲሞክራሲያዊ መብት ከመሆኑም ሌላ፣

ሀ/የተራውን ሕዝብ መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ ሠፊው ሕዝብ የሚፈልገውን ዓይነት መንግሥት ለመምረጥም ሆነ ለመቆጣጠር እንዲችል የፖለቲካ ፓርቲዎች ያስፈልጉታል።
ለ/የፖለቲካ ንቃት እንዲስፋፋ ፣የሚመረጡት የፓርላማ አባሎችም፣ለሕዝቡ የገቡትን ቃል ለሹመትና ለገንዘብ እንዳይለውጡት ለመቆጣጠር ፣በአስፈጻሚው ክፍልም እንዳይገደዱ ምክርና ለመስጠት የፖለቲካ ፓርቲዎች ያስፈልጋሉ::
ሐ/በጉሣና በሃይማኖት ከመለያየት ደረጃ አልፈን በመደብና በአስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ ድርጅቶች ለማቋቋም እንዲቻል ፣የኢትዮጵያ አንድነት ጠንካራ መሠረት እንዲኖረው ፣የብሔሮች ጥያቄ ዲሞክራሲያዊ መፍትሔ እንዲያገኝ፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉት ቅራኔዎች በመድረክ ብቻ ይፈቱ ካልተባለ የፖለቲካ ፓርቲ ያስፈልጋል::

ፓርቲ ያስፈልጋል ፣ገን እንጂ ፓርቲ ብቻ የሚሉም ሰዎች አሉ፣እንዴት ነው ሲባል ፣እንደ እንደ ታንዛኒያ፣እንደ እንደ ኪዩባ ፣እንደ ደግሞ እንደ ሶቪየት ዩኒየን፣እንዲያም እንደ ጊኒ ይላሉ፣እነዚህ ሰዎች ያለንበትን ኅብረተሰብና ያገራችንን ሁኔታና አካባቢ እያወቁም፣ወይንም እንዲሁ በበለጠ ለማታለል ይፈልጋሉ:: የሚጠቀሱት አገሮች ወደ አንድ ፓርቲ የደረሱበትን ታሪክ ረስተውና አሁን የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ያለበትን ታሪካዊ ሁኔታ ያጋጩሉ:: ባንድ በኩል ደግሞ ሲመለከቱት የገጠሩ መደብ ከሌሎች መደቦች ይበልጥ የተደራጀ በመሆኑ፣አሁን ወደ ሕዝብ በማጋደል ነው ያለውን መንግሥት፣"አንድ ፓርቲ" በሚል ፈሊጥ መሰብ እንደ ለማግባት የታቀደ [illegible] ይመስላል::በዚኑ ወቅት በኢትዮጵያ በዚህ መደቦች እያሉ አንድ ፓርቲ ይቋቋም ማለት [illegible] ጥቅም ብቻ ይጠበቅ ማለት ነው፣ስለዚህም ይህ ታሪካዊ ሁኔታ ገና አልተቋቋመ ሰዎች የሚያደርጉትን ገናና የሚከተሉትን ፣ጊዜያዊ [illegible] ጥቅም ያላቸውን ብዙ መደቦችን በተመሳሳይ ፕሮግራም ሥር በአንድነት የሚሰበስብ የፖለቲካ ድርጅት ነው::እንግዲህ የሚያሠጋው [illegible] መሠረት ሠፊ ተፈላጊ የሆነ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት በመሠረተ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማቋቋም ነው::